ስለኮሮናቫይረስ በሽታ ለሆቴል ሰራተኞች የተዘጋጀ መረጃ

በአጠቃላይ ሁላችንም ራሳቸንን እና ቤተሰቦቻችንን ከበሽታው ለመከላከል፡

እጃችንን በሳሙና እና በውሀ ቶሎ ቶሎ እንታጠብ

አይናችንን፣ አፍንጫችንን እና አፋችንን ባልታጠበ እጅ ከመንካት እንቆጠብ

ከመጨባበጥ፣ ከመሳሳም፣ ከመተቃቀፍ እንቆጠብ



ሰዎች በሚበዙባቸው ቦታዎች አንሁን፣ የግድ ከሆነም የአፍ እና የአፍንጫ መሸፈኛ እንጠቀም፣ ቢያንስ 2 የአዋቂ እርምጃ ያህል እንራራቅ

ስናስል እና ስናስነጥስ አፍ እና አፍንጫችንን በሶፍት ወይም ክንዳችንን በማጠፍ እንሸፍን

የተጠቀምንበትን ሶፍት በአግባቡ እናስወግድ

የኮሮና በሽታ የመተንፈሻ አካልን የሚያጠቃ ከሰው ወደ ሰው የሚተላለፍ ነገር ግን ሊድን የሚችል በሽታ ነው። በዚህ በሽታ የተጠቁ ሰዎች በሃገራችን መኖራቸውን ተከትሎ ሁላችንም ለዚህ በሽታ ተጋላጮች ነን።

በተለይ ደግሞ ሆቴሎች ከተለያዩ ቦታዎች የሚመጡ ሰዎችን ስለሚያስተናግዱ የቫይረሱን ስርጭት ለመግታት የተለየ ጥንቃቄ ማድረግ ያስፈልጋል።

የሆቴል አመራሮች ፣ ባለቤቶች እንዲሁም ሰራተኞች ራሳቸውን፤ ሰራተኞቻቸውን እና ደንበኞቻቸውን ከኮሮና ቫይረስ በሽታ ለመከላከል መተግበር ያለባቸው ነገሮች እና መደረግ ያለባቸው ጥንቃቄዎች አሉ።

የኮሮና ቫይረስ በሽታ ምልክቶች፡-

ትኩሳት

ሳል

ለመተንፈስ መቸገር

እንግዶች ወይም ሰራተኞች እነዚህን ምልክቶች ካሳዩ በአፋጣኝ እርዳታ እንዲያገኙ ይተባበሩ። ለተጨማሪ መረጃ 8335 ወይም 952ይደዉሉ።

ለበለጠ መረጃ
በነፃ የስልክ መስመሮች
8335 ወይም 952
ላይ ይደውሉ

የጤና ሚኒስቴር፤ ኢትዮጵያ
MINISTRY OF HEALTH, ETHIOPIA

Ethiopian Public Health Institute

በጥበቃ ሰራተኞች መደረግ ያለባቸው ጥንቃቄዎች

- የእጅ ጓንት መጠቀም
- የመፈተሻ መሳሪያዎችን በአገባቡ በአልኮል ወይም ባሳኒታይዘር ማጽዳት
- ማንኛውም ሰው ወደ ሆቴሉ ሲገባ በሳኒታይዘር እጁን እንዲያጸዳ ማድረግ
- ያለ ጓንት ከእንግዶች ጋርም ሆነ ከቁሳቁሶች (ቦርሳ፤ፓስፖርት፥ ቁልፍ) ጋር ንክኪ ካለ እጃቸውን በሳሙና እና በውሃ መታጠብ ወይም በፀረ-ጀርም ማፅጃ መጠቀም

በእንግዳ ተቀባዮች መደረግ ያለባቸው ጥንቃቄዎች

- እንግዳ ከመቀበላቸው በፊትም ሆነ በኋላ እጅን በአግባቡ መታጠብ ወይም በፀረ-ጀርም ማፅጃ መጠቀም
- ከማንኛውም እንግዳ ጋርም ሆነ ቁሳቁሶች (ፓስፖርት፥ ቁልፍ፥ ቦርሳ) ጋር ንክኪ ስለሚኖር እጃቻቸውን በሳሙና እና በውሃ መታጠብ ወይም በፀረ-ጀርም ማፅጃ መጠቀም
- እንግዶች ለመጀመሪያ ጊዜ ክፍል ለመያዝ ሲመጡ ከክፍል ቁልፍ ጋር ስለኮሮና በሽታ እና መደረግ ስላለባቸው ጥንቃቄዎች መረጃ መስጠት

በመስተንግዶ ሰራተኞች መደረግ ያለባቸው ጥንቃቄዎች

- ከእንግዶች ትእዛዝ ሲቀበሉ በተቻለ መጠን ራቅ ብለው መቆም
- የምግብም ሆነ የመጠጥ ቁሳቁሶች ለእንግዶች ከማቅረባቸው በፊት ከዚያም ደግሞ ካነሱ በኋላ እጃቻቸውን በሳሙና እና በውሃ መታጠብ ወይም በፀረ-ጀርም ማፅጃ መጠቀም
- የክፍያ ደረሰኝ፣ የአገልግሎት ዓይነት ዝርዝር/ሜኑ፣ የኢቴ ኤም ካርድ፣ የክፍያ መቀበያ ማሽን፣ ገንዘብ ወዘተ ያለ ጓንት ከነኩ እጃቸውን በሳሙና እና በውሃ መታጠብ ወይም በፀረ-ጀርም ማፅጃ መጠቀም
- የክፍያ ደረሰኝ፣ የአገልግሎት ዓይነት ዝርዝር/ሜኑ፣ የኢቴ ኤም ካርድ፣ የክፍያ መቀበያ ማሽን፣ ወዘተ የመሳሰሉትን እቃዎች በፀረ-ጀርም ማፅጃ ንፅህናቸውን መጠበቅ

በሂሳብ ሰራተኞች ወይም ገንዘብ በተቀባዮች መደረግ ያለባቸው ጥንቃቄዎች

በእያንዳንዱ የገንዘብም ሆነ የክፍያ ደረሰኝ ቅብብል መካከል ቢቻል እጅን በአግባቡ መታጠብ ካልሆነም በፀረ ጀርም ወይም በሳኒታይዘር ማጽዳት አለባቸው።